# ሹመት ሽልማት እና የማዕረግ መጠሪያዎች (የሲቪል አገልግሎትን በተመለከተ)

ጽሑፍ፣ በጌታቸው አሸኔ

እነዚህ ሦስት ቃላት አንዳንድ ጊዜ በጣምራነት ሲነገሩ ይስተዋላል፤ በሌላም ወቅት ተነጥለው ሳይደባለቁ ይነገራሉ፡፡ አለቃ ደስታ ተክለወልድ ባሳተሙት መዝገበ ቃላት፣ ሹመት (የቃሉ ምንጭ-ከግዕዙ «ሢመት») መሆኑን ትርጓሜው ክብር፣ማዕረግ፤የደረጃን እርከን ከሚገባው ክብርና ማዕረግ ጋር ሲያመለክት/ ሲያጐናጽፍ፤ ሽልማት ደግሞ ለተገኘ መልካም ውጤት የምስክርነት መግለጫ ይሆን ዘንድ ቁሳዊ ወይም መታሰቢያነት ያለው ስጦታ የሚበረከትበት ነው፡፡ ከሹመት ጋር አብሮ የሚከተል የማዕረግ መጠሪያ ሊኖር ፣ሊጣመር ወይም ላይኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰው በውጭ አገር አምባሳደርነት ተሹሞ ሳለና ከዚያም በኋላ «አምባሳደር እከሌ/እከሊት» በሚል የማዕረግ ስም የሚጠራበት ሁኔታ አለ፤በሌላ በኩል በሚኒስትርነት ደረጃ የተሾመና የነበረ፣ (ክቡር ከሚለው ተቀጥላ ውጭ) በዘላቂነት የሚጠራበት የተለየ የማዕረግ ቅጥያ ሲደረግለት አይስተዋልም፡፡

ሹመት የማዕረጉን ከበሬታ ያህል ከፍተኛ ኃላፊነትም እንደሚያስከትል ለመጠቆም መንፈሣውያን «ሢሐ-ሞት» ይሉታል፤ይህ አባባል ሹመቱን ተከትሎ ዘርፈ ብዙ ኃላፊነትን አመላካች በመሆኑ፣ተሿሚው ብርታትና ጥንካሬ እንዲኖረው የሚመኝለት ነው፡፡ ይህም ከክብሩና ማዕረጉ ይበልጥ፣ለኃላፊነቱ ቅድሚያ እንዲሰጥ የሚያሳስብ ስለሆነ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ «ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» የሚል የስግብግቦች አባባል አለ፣ይህ ብዙም ማብራሪያ የማያሻው በግልጽ ቋንቋ በተሾሙበት ዘመን በተቻለው መንገድ ተስገብግቦ መጠቀምን አጉልቶ የሚያሳይ ስንኩል አባባል ነው፡፡

ሽልማትንም በተመለከተ እንደዚሁ ተመሣሣይ አባባሎች አሉ፣ ለምሣሌም «ሽልማት ለማይገባው ሽክም ይሆንበታል» እና ሽልማት ያለቦታው ቅሌት የሚሉ ምክር አዘል አባባሎችም ይገኛሉ፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ስለ ሹመትና የሽልማት ዓይነቶች ለመተንተን ሳይሆን ጽሑፍ አቅራቢው በተለይ ስለታዘባቸው አንዳንድ ፈር የለቀቁ የሹመት ተዓማኒነታቸው አጠራጣሪ ስለሆኑ የሽልማት ዓይነቶች ለመጠቆም በማሰብ ነው፡፡

## 1- የዘውድ / የንጉሥ ዘመን ሹመቶች

ይህ ዘመን ያከተመው በ1966 ዓ.ም መጨረሻ ከቀ.ኃ.ሥ ከሥልጣን መውረድ ጋር ሲሆን፣ በነገሥታቱ ዘመን ከነበሩት የሹመት ደረጃዎች በተለይ በንጉሡ ይሰጡ የነበሩ (በነጋሪት ጋዜጣም ታትመው ይወጡ የነበሩት) በከፊል የሚከተሉት ናቸው፤

- ልዑል/ልዕልት - ለንጉሣውያን ቤተሰብና ለነገሥታት ተወላጆች/ የዘውድ ሐረግ ያላቸው መጠሪያ)
- ራስ/ (ራስ ቢትወደድ)- ባለሙሉ ሥልጣን/ የንጉሥ ወዳጅ፣ንጉሥ የሚወደው ዋና ባለሟል/የሠለጠነ ባለመብት
- ልጅ- ለመኳንንት ልጅ/ ጋብቻዎች- ለምሣሌ- ልጅ ካሣ ወ/ማርያም - (የቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት የነበሩ)
- ጸሐፊ ትዕዛዝ (በጽሕፈት ሚኒስትርነት ማዕረግ ለሚሾሙ የሚሰጥ)
- ደጃዝማች - (ባጭር አጠራር /ደጃች) ትርጓሜው - በራስና በፊታውራሪ መካከል ያለ የጦር አለቃ፣ዋና ትልቅ አዛዥ
- ፊታውራሪ -አበጋዝ/አበጋዞች-ትርጓሜው -የንጉሥ ጦር ዋና አዛዥ/አዝማች የጦር አለቃ/ፊታውራሪዎች
- ቀኛአዝማች- (ቀኛዝማች) /በጦሩ በስተቀኝ አዝማች/የጦር አለቃ
- ግራአዝማች- (ግራዝማች) /በጦሩ በስተግራ አዝማች/የጦር አለቃ
- ብላታ /ብላቴን ጌታ፤የጥቃቅኖች ሹም/አዛዥ፣መጋቢ፣ አሰልጣኝ፣ምክር አዋቂ
- ባላምባራስ- ትርጓሜው ያምባ ራስ/ጌታ፣ ዐምባ ራስን የሚያዝ፣ ከመንግሥት የተሾመ አዛዥ… ወዘተ

ከላይ በቅደም ተከተል የተዘረዘሩት የሹመት ደረጃዎች የሚያመለክቱት ከትልቁ/ከፍተኛው ማዕረግ ልዑል/«ራስ» እስከ ዝቅተኛው «ባላምባራስ» ያለውን እርከን ነው፡፡ ሹመት ሰጪው ንጉሠ ነገሥት» ከሆኑ/ሲሆኑ፣የንጉሥ ማዕረግ የሚሰየሙበትም ወቅት ነበር፡፡ ለምሳሌ፣አፄ ዮሐንስ ንጉሠ-ነገሥት በነበሩበት ዘመን፣አፄ ምኒልክ «ንጉሠ ሸዋ» ተብለው ይጠሩ

ነበር፣ንጉሥ ተክለ ኃይማኖትም የጐጃም ንጉሥ ነበሩ። በአፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘመን ደግሞ የወሎው ገዥ «ንጉሥ ሚካኤል» ተብለው ነበር።

እነዚህ የሹመት ማዕረጎች በዚያን የነገሥታት ሥርዓት የነበሩ ንጉሣዊ መሪዎች በወጣው መመዘኛ መሠረት፣ለመኳንንቱና ለታማኝ ቧለሟሎቻቸው የሚሰጡት/ የሚሰየሙበት የወቅቱ እሴትና ልዩ ትርጉም የነበራቸው/ ያላቸው ታሪካዊ ቅርሶች ናቸው፤ ስለዚህ የወቅቱ ሥርዓት እሴትና ጌጥ እንጂ፣ የኋለኛው ዘመን (ከ1967 ዓ.ም ወዲህ) ቅጥያ ስያሜ ሁነው ሊሾሙባቸው አይገባም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ፣አንዳንድ የዋኾች ክብረ -በዓልና ሌላም ሁኔታን አስታከው፣ የተጠቀሱትን ከፍተኛ የንጉሣዊ ሥርዓት የማዕረግ መጠሪያዎች (ቢትወደድ፣ ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ ወዘተ) መርጠው በመሰየም፣ በማይመለከታቸው ሥልጣንና መብት፣ ለሚሹት ግለሰብ ማዕረግ ሲሰጡ፣ ተሿሚዎቹም ይህን እሳቤ አድርገው ፣ ድል ያለ ድግስ ደግሰውና የክብር ካባ ለብሰው ፣ እድምተኛውን «ይደልዎ/ይገባዋል» ሲያስብሉና ሲያበስሩ ተስተውሏል። ሹመት ያለቦታው ይኋችኋል ይሄ ነው! ይህ አግባብነት የሌለው የታሪክ ግድፈት ነው፤ድርጊቱም ከንቱ ግብዝነት በመሆኑ የሚበረታታ አይደለም፤ ስለዚህም ከማን አንሼ በማለት ዳርዳር ያላቸው ወገኖች ሁሉ ከዚህ ዓይነቱ ያልተገባ ተግባር ሊቆጠቡ ይገባል የሚል አስተያየት አለኝ። ምክንያቱም ያለፈውን ታሪክ ሽሚያ ስለሚሆን ትርፉ ትዝብት ነው፤ውሎ አድሮም ማሾፊያ መሆኑ አይቀርም።

## 2. <u>የአካዳሚ ማዕረጎችና ሹመቶች</u>

በከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት የማስተማር ሂደቶች ውስጥ ያሉ የአካዳሚ ማዕረጎች እንደተጠበቁ ሆነው፤የተቋሙ ሴኔት በሚያወጣው መስፈርት/መለኪያ መሠረት የሚወሰኑ በመሆናቸው፣ ዝርዝር ውስጥ መግባቱ አስፈላጊ አይደለም። ከከፍተኛ ትምህርት ውጭ የሚሰጥ የአካዳሚክ ማዕረግ ስያሜ እንደ-ቅጥያ ማዕረግነት የሚገለጹበት ሁኔታ ካለ ግን፣ ከባለሙያ ጋር ያለው ተዛማጅነት ወይም አግባብነት መገምገም ይገባዋል። አግባብነት ከሌለው ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን (mass media) ወይም በሌላ የፕሮቶኮል አጠራር እንደ መታወቂያነት /ማዳመቂያነት ሊያገለግል አይገባም። ለምሣሌ፣ ኢንጂነር (Engineer) የሚለው የማዕረግ ተቀፅላ በየትኛው የትምሕርት ደረጃ /ልምድ ያሉ የምሕንድስና ባለሙያዎችን ይመለከታል፣በ (Diploma /BSc./ MSc/ Ph.D)? የትኞቹ ደረጃውን ይመጥናሉ፣ የዚህ ተቀፅላ ማዕረግ መሥፈርትና ወሳኙ አካል ማን ነው? ሙያው የሚጠበቅበትን ኃላፊነትና ደረጃውንም ለማስከበር የግድ ተመጣጣኝ እርከን ሊወጣለት ይገባል።

ከዚህ የባሰው ደግሞ በተጭበረበረ የትምህርት መረጃ (forged /defraud) በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የተሰየሙ ሰዎች በቅርቡ ሲጋለጡ ታዝበናል፤ ከመጀመሪያ ዲግሪ ያልዘለቀው ሰው የዶክተር (Ph.D.) ባለማዕረግ ሆኖ ሲጠራበትና ሲሰራበት ከርሟል፤ሌላው የተመሰከረለት የአካውንቲንግ ባለሙያ/የሒሳብ አዋቂ (Chartered Public Accountant (CPA) ሳይሆን፣ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ አቅርቦ የተጋለጠበት ሁኔታም ይወራል።

ሌላው የተከበረ የሙያ መጠሪያን በተመለከተ ሎሬት/የተከበሩ *ሎሬት የተብለው የማዕረግ ስም ከሥነ-ጥበብ /ሥነ ጽሑፍ እና የሥዕል ሙያ ጋር ተዛማጅነት እንዳለው ይነገራል። በዚህ የማዕረግ ስያሜ ከምናውቃቸውና (አሁን በሕይወት የሌሉ) እጅግ የተከበሩ ሎሬት ሜትር አፈወርቅ ተክሌና የተከበሩ ሎሬት ባለቅኔ ፀጋዬ ገ/መድህን ይመስሉኛል።

## 3. <u>የፕሮቶኮል ደረጃ መጠሪያዎች</u>

በቀድሞው ሥርዓት በጽሕፈት ሚኒስቴር እና (አሁን ደግሞ በሚኒስትሮች ም/ቤት) የፕሮቶኮል ደረጃ መጠሪያዎች ለማንና በምን ደረጃ ላይ ያሉ እንደሚሰየሙበት በግልጽ ሰፍሯል።ለምሣሌ ክቡር፣ የተከበሩ፣ ኮሚሽነር፣ አምባሳደር፣ የተሰኙት የማዕረግ ስሞች እንደ-የደረጃቸው ማን በምን ማዕረግ

* Laureate በአንድ የታወቀ የመራጭ አካል የተመረጠ ማለት ነው። አጀማመሩ በኪነጥበብ ዘርፍ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ምሑራን በተለያየ መስክ ይመረጣሉ። ለምሳሌ በኢኮኖሚክስ፣በሕክምና ... ሆነ «የዓለም ሎሬት » ብሎ መጥቀስ ግን በዓለም ደረጃ ይህን ክብር የሚሰጥ/የሚመርጥ ስለሌለ አግባብነት የለውም።

እንደሚጠራ በግልጽ ተቀምጧል፤ ስለዚህም የሚያከራክርና አሻሚ ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡

4. <u>የንግድ ሕብረተሰቡን የተመለከቱ ልዩ ልዩ ሹመቶችና ሽልማቶች</u>

በጥንቷ ኢትዮጵያ የንግድ ግብይቱ ዕቃን በዕቃ ልውውጥ (barter trade) እንደነበር ይታወቃል፡፡ ዘመናዊው የንግድ አሠራር የተጀመረው በአፄ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት እንደነበር ጥር 1973 ዓ/ም የታተመው ንግድና ልማት ጋዜጣ ቁ.8 ያወሳል፡፡ ዘመናዊውን ንግድ ከጀመሩት ነጋዴዎች መካከል አርመኖች፣ ፈረንሣዮች፣ ግሪኮች፣ ዓረቦችና ሕንዶች ተጠቃሽ ሲሆኑ ቀስ በቀስ ኢትዮጵያውያን፣በተለይ ከጅማና ከወሎ የመጡ ነጋዴዎች ዘመናዊውን የንግድ ሥራ እንደተቀላቀሉ ተገልጿል፡፡

ከዚህ በላይ የዘመናዊውን ንግድ ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ ያነሳሁት ያለ ምክንያት አይደለም፤ ምክንያቱም ከዚያን ጊዜ ወዲህ እንደተጀመረ ስለሚወሳለት «የንግዱ ሕብረተሰብ » የማዕረግ ስሞች ለመጥቀስ ብዬ ነው፡፡ ከተጠቃሽ ስሞች መካከል አንደኛው «ነጋድራስ» የተባለው የማዕረግ ስም ሲሆን፣ይህ የማዕረግ ስም በዘመኑ መንግሥት (በንጉሡ ፈቃድ) የሚሰጥ፣ ትርጓሜውም «የነጋዴ አለቃ የበላይ፣ ከመንግሥት የተሾመ» ለማለት ነው፡፡ ሌላው የሹመት መጠሪያ በጅሮንድ የተባለው ሲሆን፣ይህም የከበረ ዋጋ ያላቸው የወርቅና የብር አፍሳሾችና ያንጥረኞች አዛዥ፣ዋና የገንዘብ ሹም/ግምጃ ቤት፤የሆነ የታማኝ ሰው ሹመት ነው፡፡ ይህ የቀድሞው ዘመን ማዕረግ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ ዘርፈ- ብዙና ድንበር-ዘለል የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ብዙ ለውጥና የውጭ አህጉራት ተጽእኖ በመታከሉ የኃላፊነት ደረጃ የማዕረግ ስሞች ተከልሰው ይገኛሉ፡፡ በቅርብ ጊዜ እንኳን ከተከለሱት የሹመት መጠሪያዎች መካከል «ፕሬዝዳንት» እና «ዋና ሥራ አስፈፃሚ» Chief Executive Officer/ CEO የሚባሉት የበፊቱን «ዋና ሥራ አስኪያጅ» ተክተውት ይገኛሉ፡፡

እዚህ ላይ ማንሳት የፈለግሁት የሹመቱን ዓይነት ሳይሆን፣ ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ መልክ የሚስተዋለውን የድንበር ዘለል ተቋማት ሽልማትና ማዕረግን የሚመለከት ነው፡፡ አንደኛው ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ ሲሆን፣ በሚባልለት መስክ በቂ የኮርስ ዝግጅት፣ መምህራንና አስተማማኝ እውቅና /academic accreditation/ ሳይኖራቸው በማስታወቂያ ጋጋታ ብቻ ሰዎችን በመመሰጥ እያግባቡ፣ ለእውቀት ማግኛ ሳይሆን፣ ለምሥክር ወረቀት (ዲግሪ) መነገጃ በየአህጉራቱ የተቋቋሙትን (ከፊሎቹም ከግለሰብ መኖሪያ ቤት የሚካሄዱትን) የሚመለከት ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከእንደዚህ ዓይነት ተቋማት በተገኘ ማዕረግና ሽልማት ሲኩራሩ ይስተዋላል፣ ቁምነገሩ ከወረቀቱ ሆነና! ሌሎች ደግሞ ለCV ማዳበሪያና ለቅጥር ወይም ደረጃ እድገት ይጠቀሙበታል፡፡ ይህ ሁኔታ ባንድ የከፍተኛ ትምህርት ምርቃት ወቅት፣ ቀ.ኃ.ሥላሴ ያስተላለፉትን መልዕክት ልብ እንድንለው ያስታውሰናል፤ የተናገሩትም «በ**ሥራ ያልተገለጸ ዕውቀት፣ ካለማወቅ አይሻልም** »ብለው ነበር፡፡

ቀደም ሲል የትምህርት ሚኒስቴር «የከፍተኛ ትምህርት የምሥክር ወረቀት» (በተለይ ዲግሪን በተመለከተ) የደረጃ የመጣጣኝነት ምዘና ዋና ክፍል እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ የዚህ ዓይነቱ ምዘና ሰፋ ባለ መልክ የምሥክር ሰጪውን ተቋምና የትምህርት ጥራቱን ዘልቆ የሚመረምር በመሆኑ፤ በዘለቄታዊነት ለእውነተኛ ትምህርት ፈላጊዎችም ሆነ ለቀጣሪ ድርጅቶች የሚሰጠው መረጃ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡ በአሁኑም ወቅት የተመጣጣኝነት ምዘና መጠናከር ያለበት

ጉዳይ ነው፣ይህ ቢሆን ኖሮ፣ባለፈው ዓመት መነጋገሪያ የነበረው፣ የዶ/ር ኢንጂ.ሣሙኤል ዘሚካኤል ዓይነቱ በእንጭጩ ይጋለጥ በነበር! አሁንም ሊታሰብበት ይገባል፡፡

ቀጥሎ የንግዱን ሕብረተሰብ በከፊል በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚያማልለው የውጤታማነት ሰርተፍኬት በወርቅ ደረጃ እና በአልማዝ ደረጃ (Certificate of High Achievement - Gold Standard/Diamond Standard) በሚል በተሞካሸ ቋንቋ ስላንድ (ብዙም ጠልቀው ስለማያውቁት) ድርጅት በመጻፍና በማግባባት፣ከላይ ለተጠቀሰው የሽልማት ደረጃና ክብር የተመረጡ መሆኑን በአድናቆት የሚገልጹበት ሁኔታ ነው፡፡ እነዚህ የሽልማት ድርጅቶች በውጭ አገር በተለይም በአውሮፖ የተቋቋሙ ሲሆን፣በሌሎች አገር ያሉትን የዋህ የድርጅት ባለቤቶች/ሥራ መሪዎችን በማጥመድ፣ ከድረ-ገጽ የተቀነጨበን ተግባር (profile) አጉልተውና አዳንቀው በማቀረብ፣ለልዩ ሽልማትና ማዕረግ የተመረጡ መሆኑን ያበስራሉ፡፡ በመቀጠልም በክብረ በዓሉ ላይ ተገኝተው የተጠቀሰውን የክብር ሽልማት እንዲቀበሉ በመጋበዝ፣ የሥነ-ሥርዓቱን ድምቀት፣ የተካፋዮችን ስብጥርና ብዛት፣ የሚካሄድበትን ቀንና ከተማ ይገልፃሉ፡፡ አያይዘውም ለአጠቃላይ ዝግጅቱ (ለዋንጫው፤ ለሠርተፍኬት፤ የእራትና የአንድ ምሽት የሆቴል አዳር፤ወዘተ) ከ3500

ዶላር እስከ 5000 ዶላር ቅድሚያ ክፍያን ይጠይቃሉ። ይህ ክፍያ በቅድሚያ ገቢ ካልተደረገ በበዓሉ ላይ መገኘት አይቻልም፤ባለጉዳዩ ባይመቸው እና የተባለውን የእውቅና ሰርተፍኬት ላኩልኝ ቢል እንኳ አይልኩለትም።

ይህን ጉዳይ ያለምክንያት አላነሳሁትም፤ከ13 ዓመት በፊት (Sep.2002) ቢ.አይ.ዲ (Business Initiative Directions/B.I.D) የተባለ፣ ቢሮው ማድሬድ፣ ስፔይን የሆነ፣ ባካሄዳቸው ዘርፈ ብዙ መመዘኛዎችና መሥፈርቶች መሠረት፣ በእኔ ሥራ-አስኪያጅነት የሚመራው ድርጅት፣«ለዓለም- አቀፍ የሥራ -ጥራት የክብር ሽልማት በወርቅ ደረጃ» (International Quality Crown Award in Gold Category) የተመረጠ መሆኑን በመግለጽ ሞቅ ያለና አድናቆት የሞላበት ደብዳቤ በፖስታ ሜጥን አድራሻ ይልክልኛል። በተለይ በደብዳቤው መጀመሪያ ገጽ ላይ የተመለከተውና (How your Co. was selected?) በሚል የቀረበው የምሥክርነት ቃል፣የድርጅቴን አቋም ያለአግባብ ያገዘፈ ማመኳሻ ነበር። ሰውም ሆነ ድርጅት መሞካሸት ላይጠላ ይችላል፣በበኩሌ ግን ሚዛናዊነት የጎደለው መደለያ መሆኑን በመረዳቴ ቀልቤን አልሳበውም። አቅሙም ቢኖረኝ በሽልማት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ አልተገኘሁም።

ላለፉት ብዙ ዓመታት በርከት ያሉ የድርጅት ባለቤቶችና ሥራ መሪዎች ተመሣሣይ የሽልማት ጥሪዎች እንደደረሳቸው ተረድቻለሁ። አንድ ወዳጄ የሆነና ባንዱ የሽልማት ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኘ ስለ ሁኔታው ሲገልጽልኝ፣ «በሕይወት ዘመኑ እንደዛ ዕለት ተደስቶ እንደማያውቅ፣» የደስታውን መጠን አግዝፎ በመናገር ነበር። ይህን የአመለካከት ልዩነት ታዝቤአለሁ።

## 5. ሌሎች ሙያ ነክና ልማዳዊ የሆኑ ቅጥያ መጠሪያዎች

በዘልማድ ከሚጠቀሱ የስም ቅጥያዎች አንዱ «አርቲስት» (artist) እከሌ እየተባለ ያለገደብና መስፈርት ከወጣት እስከ አዛውንት እድሜ ክልል ያሉ ፣መድረክ ተዋናዩ፣ ሙዚቀኛው፣ ኮሜዲያን ነኝ ባዩ፣ ወዘተ በጅምላ የሚሰየሙበት መጠሪያ ሆኗል። በተመሣሣይም ሁኔታ ደራሲ እከሌ፣ገጣሚ እከሊት፣ ሃያሲ፣ፀሐፊ ተውኔት፣ወዘተ እየተባሉ በቅጥያ ሥም በብዛት የሚጠሩ እየተስተዋለ ነው፤ለስያሜው ተቀባይነት የወጣ መስፈርት አለ ወይስ በዘፈቀደ የሚለገስ ነው? ምን አለ ለሙያው ከበሬታና እውቅና ሲባል የሙያው አባላት በሙያ ማህበራቸው አማካኝነት መሥፈርት፣ደረጃና እርከን ቢያስቀምጡለት ?

በቅርቡ ደግሞ ከወትሮው ለየት ያለ «የተከበሩ የሰላም አምባሳደር» የሚል የቅጥያ ስያሜን ሰምቼ አግባብነቱ ግርታን ፈጥሮብኛል።ታዋቂ ሰዎች «የክብር አምባሳደር» ተብለው የሚሰየሙበት አጋጣሚ እንዳለ አውቃለሁ፣ ለምሳሌም የተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መርጃ (UNICEF) የሚሰይመው አንዱ ነው፤ከዚህ በዘለለ መልክ ግን አንድ ግለሰብ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚሰይመው ውጭ) በምን መስፈርት ነው በአምባሳደርነት ማዕረግ ሊጠራ የሚችለው? ያልሆኑትንና ያልከወኑትን ማዕረግ መሻማት «ሳይገድሉ ጎፈሬ!» ነውና ቢቀር ይበጃል!

## ማጠቃለያ

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በመጀመሪያ ሰዎች በተቻለ መጠን «እውነትን» በትክክል አውቀውና አክብረው በመኖር ከግብዝነት ፀድተው እንዲገኙ፣ ያልሆኑትንና የማይመጥናቸውን ከንቱ ውዳሴ በመሻት ራሳቸውንም ሆነ ሌላ የማይገባውን ሰው እንዳይሰይሙ፤ መጽሐፉ እንዳዘዘው «የቄሣርን ለቄሣር፣ የእግዜአብሔርንም ለእግዚአብሔር» ያደርጉ ዘንድ ለማሳሰብ ነው። በመቀጠልም ታሪካዊ መሠረት ያላቸውን የማዕረግና የክብር ስሞችን በማዛባት እንዳያቃልሉና፣እንዲያከብሩ ምክር ለመለገስ፣ በሌላ በኩል አብዛኛው ሰው የሚያደርገው የትምህርት ክትትልና ጥረት የሚበረታታ ሆኖ ሳለ፤ ዓላማው ግን የተዛባና የተቀባባ ደካማ የምስክር ወረቀት ማግኘት ላይ ሳይሆን፣ ዘለቄታዊ እውቀት የሚሸመትበትን ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ ለማሳሰብ ነው።

## ዋቢ መጽሐፍትና የመረጃ ምንጮች


1- ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት - አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ / አርትስቲክ ማተሚያ ቤት -1962 1ኛ እትም
2- ንግድና ልማት ጋዜጣ (ጥር 1973 ዓ.ም ቁ.8) በመጥቀስ የን.ሥ.ት.ም.ማህበር ሰኔ 1979 እትም የተቀዳ
3- ኢኮኖሚክ ሒስትሪ ኦፍ ኢትዮጵያ-ፕሮ. ፓንክረስትን በመጥቀስ ንግድና ልማት ጋዜጣ (ጥር 1973 ዓ/ም ቁ.8 ያተመ